# ከትምህርት ቤቶች አለቃ(Superintendent)የተላከ መልዕክት

## *ለ 2021-2022 የትምህርት ዘመን(ዓመት)ዝግጅት*

ውድ የኤድመንድስ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት (አውራጃ) ቤተሰቦች ፣

መልካም የበጋ ጊዜ እያሳለፋችሁ እንደሆነና የ2021-2022 የትምህርት ዘመንን በጉጉት እንደምትጠብቁት ተስፋ አደርጋለሁ። የዲስትሪክቱ (የትምህርት ቤት አውራጃው) አመራሮች ጠንክረው እየሰሩና ፣ ተማሪዎቻችን ወደ ትምህርት እንዲመለሱ በጉጉት እየተዘጋጁ ነው።

ከዚህ በታች ለሰማናቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ስለጤና፣ ደህንነትና ለመጪው ትምህርት ዓመት ዋና ዋና ቀናት፣ አሁን የተሻሻለውን የትምህርት ቤት የመጨረሻ ቀን ጁን 24 2022 (June 24, 2022) ይጨምራል

ተማሪዎቻችንን በቅርቡ ሲመለሱ በመልካም ለመቀበል በጣም ደስተኞች ነን

ከአክብሮት ጋር

ዶ/ር ገስታቮ ባልዴራስ
ከትምህርት ቤቶች ተቆጣጣሪ
Dr. Gustavo Balderas
Superintendent

## ኮቪድ-19 (COVID-19) ጤና እና ደህንነት

***የተማሪዎቻችን፣ ቤተሰቦችን እና ሠራተኞቻችን ጤንነትና ደህንነት ቅድሚያ የምንሰጠው ነው***

ለተማሪዎቻችን ፣ ለሠራተኞቻችን ፣ ለቤተሰቦቻችን እና ለማህበረሰባችን ጤና እና ደህንነት የምንችለውን ሁሉ እያደረግን መሆኑን ለማረጋገጥ የኤድመንድስ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ከዋሽንግተን ስቴት (ግዛት) የጤና መምሪያ (DOH) እና የስኖሆሚሽ የጤና ድስትሪክት (አውራጃ) (SHD) የቅርብ ጊዜውን መመሪያ ይከተላል። በትምህርት ዘመኑ ( ዓመቱ) ውስጥ ማንኛውም አዲስ መመሪያ ከ DOH እና SHD ጋር እናስተካክላለን።

**በሕንፃዎቻችን ውስጥ ላሉት ሁሉ ጤና እና ደህንነት፡-**

- ጭምብል ማድረግ (መልበስ)ግዴታ ነው
- አካላዊ ርቀትን መጠበቅ
- ትምህርት ቤት ወይም የድስትሪክት (የአውራጃ) ሕንፃ ከመድረስዎ በፊት ለኮቪድ -19 ሕመም ምልክቶች ይመርምሩ።
- ሕህመም ከተሰማዎት ቤት ይቆዩ

**የኮቪድ -19 (COVID-19) የጤና እና ደህንነት መመሪያ መጽሐፍ**

የ 2021-22 የኤድመንድስ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት (አውራጃ)የኮቪድ-19(COVID-19) የጤና እና ደህንነት መመሪያ መጽሐፍ በድረ ገጺያችን ላይ ይገኛል: bit.ly/ESDCOVIDsafety

.

የዋሽንግተን ስቴት (ግዛት) የጤና መምሪያ (DOH) እና/ወይም የስኖሆሚሽ የጤና ድስትሪክት (አውራጃ) (SHD)ማሻሻያ ካወጡ የመመሪያ መጽሐፋችንን ላይ መሻሻያ እናደርጋለን። የመመሪያ መጽሐፋችንን ጠንቅቃችሁ በማወቅ የኮቪድ-19 ስለመቆጣጠር የጤናንና ደህንነትን ዕቅድ በተመለከተ ለሚኖራችሁ የሎጅስቲክ ጥያቄዎች መልስ ልታገኙ ትችላላችሁ።

## ዕለታዊ የጤና ምርመራዎች

ለ 2021-22 የትምህርት ዓመት የዋሽንግተን ግዛት (ስቴት) የጤና መምሪያ ለእያንዳንዱ ተማሪ እና ሰራተኛ አባል በዚህ ጊዜ የዕለት ተዕለት የጤና ምርመራ ማረጋገጫ አያስፈልገውም። ሆኖም ፣ የኤድመንድስ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት (አውራጃ)ሁሉም ቤተሰቦች ተማሪዎቻቸውን ትምህርት ቤት ወይም የድስትሪክቱ (አውራጃ) ሕንፃ ከመምጣታቸው በፊት የኮቪድ-19 (COVID-19) የሕመም ምልክቶች እንዲመረምሩ ይጠይቃል። ሰራተኞች ከመምጣታቸው በፊት ተመሳሳይ የጤና ምርመራ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የሕመም ምልክቶችን ዝርዝር በድረገጢያች ላይ COVID-19 symptoms on our website. ይመልከቱ። ተማሪዎች ለኮቪድ-19 (COVID-19) ከተጋለጡ ፣ የኮቪድ -19ሕመምም ምልክቶች ካሉባቸው ወይም በሌሎች በሽታዎች ከታመሙ ተማሪዎችን ቤት ውስጥ ማቆየት አለባቸው።

## ተጨማሪ የጤና እና የደህንነት መቆጣጠሪያዎች

- **ማፅዳት እና እንዳይበከል ማድረግ፦**
  በብዛት የሚጠቀሙባቸውን አካባቢዎች እና ቦታዎች ለከፍተኛ ኤሮሶል ወይም የሰውነት ፈሳሶች ሊፈጠሩባቸው የሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ ያተኮረ የተደጋጋሚ የፅዳት ሒደት
- **በሁሉም የድስትሪክት (የአውራጃ) ትምህርት ቤቶች እና ሕንፃዎች ውስጥ ከፍተኛ የአየር ማናፈሻ እንዲኖር ማድረግ፦**
  የኤችቪኤሲ (HVAC) ወደ ህንፃዎች የሚገባውን የውጭ አየር መጠን ከፍ ለማድረግ እና የተሻሹሉ የአየር ማፅጃ ወንፊቶች የገቡና በየጊዜው የሚቀየሩ እንድሆኑ ተደርጓል
- **የእጅ ንፅህና፦**
  ተማሪዎችና ሰራተኞች እጃቸውን ሕንፃ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት እጃቸውን እንዲታጠቡ ወይም በሳኒታይዘር ማፅዳት ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ቀኑን ሙሉ በተደጋጋሚ እጃቸውን መታጠቡ ወይም በሳኒታይዘር ማፅዳት ይኖርባቸዋል። የጀርም መሰራጨትን ለመከላከል ይህንን እጅዎን እንዴት በትክክለኛ መንገድ እንደሚታጠቡ ***how to properly wash your hands*** የሚለውን ቪዲዮ ይመልከቱ
- **ጭምብል በትክክል ማድረግ (መልበስ)**
  በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ጭምብል በትክክል ማድረግ (መልበስ)ግዴታ ነው። ጭምብልን በትክክለኛው መንገድ ስለመልበስ፣ ስለማድረግ እና ማውለቅ የሚለውን ይህንን ***how to properly wear, put on and take off your mask***. ቪዲዮአችንን ይመልከቱ
- **የምሣ ሰዓት ደህንነት፦**
  በግዛቱ (ስቴቱ) የጤና መምሪያ ክፍል መሠረት በተቻለ መጠን ድስትሪክታችን (አውራጃችን) በተቻለ መጠን ምሳ በሚበሉበት ወቅት በትንሹ በ6ስት ጫማ ርቀት እንዲቀመጡ እናደርጋለን። እንያንዳንዱ ት/ቤት የምሳ ሰዓታቸው እንዴት እንደሚሆን የየራሳቸው ዕቅድ ይኖራቸዋል። ይህንንም መረጃ ት/ቤት ከመከፈቱ በፊት ለወላጆች ያጋራሉ
- **አንዴ ከተጀመረ በኋላ ትምህርት ቤቶች ክፍት የሚሆኑት ለተማሪዎች እና ለድስትሪክቱ (ለአውራጃ) ሠራተኞች ብቻ ይሆናል።**
  ግቢያችን ከት/ቤት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች ዝግ ይሆናል። ***ይህም ቤተሰብንና የማህበረሰቡ ወዶ ፈቃደኞችን ይጨምራል።*** ነገር ግን የት/ቤታችን ዋና ቢሮዎች አጣዳፊ ችግር ላጋጠማቸው የቤተሰብ አባላት ክፍት ይሆናል። በዚህ የትምህርት ወቅት ሠራተኞቻችን ሊኖሯችሁ የሚችሉ ጥያቄዎች በሙሉ በስልክ፣በኢሜይል ለመርዳት ዓመቱን በሙሉ ዝግጁ ናቸው። ሕንፃችን የሚገቡትን ሰዎች ቁጥሩን ለመመጠን ብንሞክርም የትምህርት ቤት ቢሮ መምጣት ቢያስፈልግዎት እባክዎ እነዚህን ያስታውሱ፦

  - በግቢያችን በማናቸውም ጊዜ ጭምብል ማድረግ (መልበስ) ግዴታ ነው
  - አካላዊ ርቀት መጠበቅን ይለማመዱ
  - ምንም ዓይነት ሕመም ከተሰማዎት ወደ ግቢያችን አይምጡ

## የኮቪድ-19 (COVID-19) ክትባት

በአሁኑ ጊዜ የኮቪድ-19 ክትባት 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ላሉ ሰዎች ይገኛል (ይሰጣል)። ስለክትባቱ የበለጠ ለማወቅና ቀጠሮ ለመከተብ እንዴት እንደሚያዝ የስኖሆሚሽ የጤና አውራጃ ድረገፅን በ Snohomish Health District’s website እንዲመለከቱ እናበረታታለን

## የኮቪድ-19 (COVID-19) ምርመራ

ድስትሪክታችን(አውራጃችን) የኮቪድ-19 (COVID-19) ምርመራ ለተማሪዎቻችን (በቤተሰብ ፈቃድ)እና ለሠራተኞቻችን ለኮቪድ-19 ለተጋለጡ ወይንም የኮቪድ መሰል ሕመም ምልክቶች ከተሰማቸው በነፃ እንሰጣለን። ከጭምብል ማድረግ በተጨማሪ የኮቪድ ምርመራ ማድረግ ችግሩ እንዳይበዛ የማድረግ ዋነኛው መንገድ ነው። ምርመራ በሁሉም የአውራጃው ትምህርት ቤቶች ይሰጣል።

## የሥነጥበብ ሥራ

የዋሽንግተን ግዛት (ስቴት) የጤና መመሪያ ሁሉም ተማሪዎች የመረጧቸውን የሥነጥበብ ኮርስ(ዎች)የመሳተፍ ዕድል እንዲኖራቸው ያረጋግጣል። እባክዎን ከጤና መምሪያ ክፍል (DOH)ወቅታዊ የሆነውን መመሪያበ bit.ly/ESDCOVIDsafety ይመልከቱ።

## የበልግ ወቅር (ፎል-Fall) አትሌቲክስ

የተማሪዎችን አትሌቲክስ በተመለከተ የግዛቱን (የስቴቱን) እና የካውንቲውን መመሪያዎችን እንከተላለን። በአሁኑ ጊዜ የሁሉም የበልግ አትሌቲክስ የከፍተኛ መካከለኛ ተ/ቤት ተማሪዎች መሳተፍ ይችላሉ። ቁልፍ የሆኑትን የበልግ ቀኖች፣የእስፖርት አማራጮች፣ቅፆች እና ብቁነት በ bit.ly/ESDAthleticsUpdate በኮማፒተር ላይ (ኦንላይን)ይመልከቱ።

## የቀን መቁጠሪያ፡--2021-22 የትምህርት ዓመት ዘመን(ዓመት)




የቤተሰብና የማህበረሰብ ቀን መቁጠሪያ ላይ ለውጥ አለ። ***አሁን የትምህርት ቤት የመጨረሻው ቀን አርብ June 24, 2022 ነው*** አስፈላጊ ከሆነ በበረዶ ምክኒያት ለሚቋረጡ የትምህርት ቀናት መተኪያ በቅደም ተከተል እንደዚህ ይሆናል

- ፍብሩዋሪ 22 2022
- ማርች 18 2022
- ጁን 27 2022
- ጁን 28 2022
- ጁን 29 2022

የመጨረሻው የተሻሻለው የቀን መቁጠሪያ ኩነት ሁልጊዜ በዲስቲሪክቱ (አውጃውa) በኮምፒውተር ላይ ( የኦንላይን) ቀን መቁጠሪያ በ bit.ly/ESDCalendar ላይ ይገኛል።

## የትምህርት ቤት የመጀመሪያው ቀን፡- ረቡዕ ሴፐቴምበር 8 2021

ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ በአካል ቀርበው እና በኮምፒውተር መስመር ላይ (በኦንላይን) የሚማሩ ተማሪዎቻችንን ረቡዕ ሴፕቴምበር 8 ለመቀበል ደስተኞች ነን። ***የመዋለ ሕጻናት ተማሪዎች ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ቀን ሰኞ ሴፕቴምበር 13 ይሆናል።***

## የትምህርት ቤት አውቶቡስ ይጠቀማሉ?

***እባክዎን ያስተውሉ: ሁሉም ተሳፋሪዎች እና ሹፌሮች በትምህርት ቤት አውቶቡሰ ላይ ሲሆኑ ጭምብል ማድረግ ግዴታ አለባቸው።***

የአውቶቡስ ማቆሚያ እና የመንገድ መስመር መረጃ ከሰኞ ኦገስት 23 ጀምሮ በስካይዋርድ ( Skyward): በ bit.ly/ESDSkywardaccounts ውስጥ ይገኛል

**አዲስ የተማሪ አውቶቡስ መረጃን ማግኛ መንገድ**

*የኤዱሎግ ፓሬንት ፓርታል አፐ ( **Edulog Parent Portal App)** ለቤተሰቦች የተማሪዎቻቸውን የአውቶቡስ መስመርና የመንገድ ለውጦችና ማሻሻያ የመረጃ ማግኛ መንገድ ነው። የልጅዎ የተለየ የአውቶብስ መሥመር እስከ ኦገስት 23 የማይወጣ ቢሆንም ይህንን አፐ (APP) እንዲያወርዱና አዲሱን ዲጂታል መሣሪያ እንዴት እንደሚጠቀሙ እንዲያውቁ አጥብቀን እናበረታታለን። መተግበሪያውን ከዚህ ጋ:* bit.ly/ESDParentPortal *ያውሩዱና እና የእርስዎን መለያ አካውንቶን ይክፈቱ።*

## ልጅዎን ስለማድረስ እና ስለማንሳት

ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ሠራተኞች የመኪናም የእግረኛም ትራፊክ እንዴት እንደሚቆጣጠሩ የሚያስረዳ ማስረጃ ትምህርት ቤትዎ ያካፍልዎታል። በአሁኑ ወቅት ቤተሰቦችና ጎብኝዎች ትምህርት ቤት ውስጥ መግባት ስለማይፈቀድላቸው ተማሪዎቻቸውን በተመደበላቸው የማንሻ ዞን ማድረስና ማንሳት ይኖርባቸዋል።

## ነፃ ቁርስና ምሣ ለሁሉም ተማሪዎች!

ለምሣ ስለመክፈልም ሆነ ምሣ ስለመቋጠር ከአሁን በኋላ መጨነቅ የለብዎትም። ለ2021-2022 የትምህርት ዘመን (ዓመት) ለሁሉም ተማሪዎች ምግብ በነፃ ይሰጣል! የምግብ ዝርዝሩ (ሜኑ)መረጃ ሰኞ ከኦገስት ጀምሮ በ bit.ly/ESDmenus ላይ ይቀርባል

## ቤተሰብዎ የገንዘብ እርዳት ያስፈልገዋል??

በ2021-2022 የትምህርት ዓመት ለሁሉም ተማሪዎች ቁርስ እና ምሣ በነፃ የሚቀርብ ቢሆንም ብቁ ለሆኑ ተማሪዎችና ቤተሰቦች የነፃ እና ቅናሽ ምግቦችን የማግኛ ማመልከቻን ቅፅ እንዲሞሉ እናበረታታለን። ይህንን ማመልከቻ መሙላት ተማሪዎች የኮርስ ክፍያዎች እና የስፖርት ክፍያዎች የገንዘብ ድጋፍ ፣ እንዲሁም ለበይነመረብ (ኢንተርኔት) የዋጋ ቅናሽ የመሳሰሉ ተጨማሪ ጥቅሞችን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ማመልከቻዎች እዚህ bit.ly/ESDFinancialsupport ይገኛሉ።

የወረቀት ማመልከቻ ለመጠያቅ በስልክ ቁጥር 425-431-7077 ይደውሉ።

## የተማሪ የሕክምና መዝገብ መስፈርቶች

ሁሉም ተማሪዎች (**በአካል ወይም በኮምፒውተር በመስመር ላይ ፕሮግራሞችን የሚሳተፉ**) በጣም ወቅታዊ የሆነውን የክትባት መዝገቦቻቸውን ማቅረብ አለባቸው። ይህም መዝገብ በሕክምና መረጋገጥ አለበት። ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የትኞቹ ክትባቶች እንደሚያስፈልጉ የበለጠ ለማወቅ ፣ እባክዎን የተማሪ ጤና አገልግሎት ድር ጣቢያችንን በbit.ly/ESDImmunizations ይመልከቱ

## ስካይዋርድ (Skyward): የተማሪዎን የትምህርት መዝገቦችን እና የትምህርት ቤት መረጃ ለማግኘት

እኛ ሁሉም ቤተሰቦች ስካይዋርድን (Skyward) bit.ly/ESDSkywardaccounts በደንብ እንዲያውቁ እንዲረዱ እናበረታታቸዋለን

ይህ የድስትሪክቱ(የአውራጃው) መዝገቦች ስርዓት ነው ፣ እና የሚከተሉትን ያጠቃልላል

- ውጤቶችን
- የቤተሰብን ማግኛ መረጃዎችን
- የአውቶብስ የመንገድ መስመር መረጃዎችን
- እናም ሌሎችም!

## We are hiring, apply online today! እኛ እየቀጠርን ነው ዛሬ በኮምፒውተር በመስመር ላይ (በኦንላይን)ያመልክቱ!

የኤድመንድስ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት (አውራጃ) ይቀላቀሉ! እባክዎን ለክፍት የሥራዎች ቦታዎች ድረጣቢያችንን በ bit.ly/ESDJobs ይመልከቱ

በተለይ የትምህርት ቤት አውቶብስ ነጂዎች (ሹፌሮች) እና የምግብ አገልግሎት ሠራተኞች እንፈልጋለን።